## ይኸንን አላዩ!



ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ፣
የብርዝ የዘመራ መጥመቂያ ጋኖቹ፣
በሊጥ ተጨማልቀው ሲመጡ ቶሮቹ፣
ምንቸት ገንቦዎችን ጽዳት ሊያስተምሩ።

ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ፣
መምህር አካለ ወልድ አራት ዓይናው ጎሹ፣
የልጅ ልጆቻው ወርደው ተመንበሩ፣
ደንብ ሥርዓትን ጨዋነት ሲማሩ፣
አራስን ቀጥቅጠው አርደው ተሚገሉ::

ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ፣
ሃጂ ሼክሆቹ ተደሴ ተቃሉ፣
የሰው ልጅ ዘቅዝቀው አርደው የገፈፉ፣
አማራን ሰውነት ሽቅብ ሲያስተምሩ።

ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ፣
አቡነ ሚካኤል አቡነ ጴጥሮሱ፣
መስቀልን ጨብጠው ፓትሪያርክ ጳጳሱ፣
ተነጭ አሽከር ፓስተር ትዕዛዝ ሲቀበሉ!

ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ፣
አድማሱ ጀምበሬ ጎርጎሪዎስ ሊቁ፣
የነፍስ ልጆቻቸው በመንፈስ ሲዘቅጡ፣
ፓስተር ሽቅብ አይተው አቤት! አቤት! ሲሉ!

ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ፣
ሊቀ-ጠበብት በላይ መሪጌታ አለሙ፣
እነ ዳንኤል ክስረት እነ ሆድ አምላኩ፣
እንደ ግብር መውጫ እያውደለደሉ!
ለሰላዩ ፓስተር ራቦል ሲጥፉ።

ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ፣
መምህሬ ኤርምያስ ጎንደር የቁስቋሙ፣
ታማኝ ካህን ጠፍቶ አልቦ ዘመድ ያሉ!

ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ፣
አቡነ ባስልዮስ ቴዎፍሎስ ሰማእቱ፣
ካድሬ ይህ አድጎች ክህነት ሲያቆሽሹ።

ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ፣
ሊቅ መሀሪ ትርፌ ተዋናይ ጠቢቡ፣
የዘሩትን ቅኔ ቁራዎች ሲለቅሙ።

እሙሃይ ገላነሽ ይኸንን አልሰሙ፣
ተማሪዎቻቸው ለጉድ ሲሰበኩ፣
ሥለ ክብር ማእረግ በአብዮት ፓስተሩ።

ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ፣
እነ አለቃ አያሌው ሆሜር የግሪኩ፣
እነ አብይ አህመድ ወደ ላይ ሲሸኑ፣
አማራውን ፍትህ ሥርዓት ሊያስተምሩ።

ይኸንን አልሰሙ ይኸንን አላዩ!
ጆግኖች አርበኞቹ አገር ያስረከቡ፣
ልጆቻቸው ሰንፈው አባት ሲያሰድቡ!

ይኸንን አላዩ!

**በላይነህ አባተ** (abatebelai@yahoo.com)
*ታህሳስ ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.*